ውድ ወላጅ/አሳዳጊ፤

በ2009 ዲሲ (District of Columbia)፤ ዲሲ ህግ 17-10 የሂውማን ፓፒሎማቫይረስ ክባቶች እና ማሳወቅ የ 2007 ህግ (DC Law 17-10 Human Papillomavirus Vaccinations and Reporting Act of 2007) የሚባል እና ለመጀመሪያ ጊዜ በዲሲ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚመዘገቡ ከ6ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሳዩ ማስረጃዎችን ማቅረብ እንዳለበት የሚያዝ ህግ አጽድቋል።

1. የሂውማን ፓፒሎማቫይረስ (Human Papillomavirus (HPV)) ክትባት፤ ወይም

2. በዚህ የትምህርት ዓመት የኤችፒቪ እትባት በሚከተሉት ምክንያቶች ያለወሰደ መሆኑን፤

a. ወላጅ ወይም አሳዳጊ ተቃውሞ ያላቸውና ክትባቱ ያሃይማኖት እምነቱን የሚቃረን መሆኑን በጽሁፍ ለትምህርት ቤቱ ዋና አስተዳዳሪ በማሳወቅ፤
b. የተማሪው ሃኪም ውይም የሃኪም ተወካይ ወይም የህዝብ ጤና ባለስልጣናት ክትባቱ በጤና ምክንያት የማይመከር መሆኑን ለትምህርት ቤቱ የጽሁፍ ማረጋገጫ በማቅረባቸው፤ ወይም
c. ወላጅ ወይም አሳዳጊ ወይም የህግ አሳዳጊ የኤችፒቪ ክትባት (HPV) አስፈላጊነት ተነግሮት ነገር ግን የክትባት መርሃ-ግብሩን አለመውሰድ መምረጡን በፊርማ በማረጋገጥ።

በየዓመቱ የጤና እንክብካቤ ሰጪዎች ከ 32,000 በላይ ከኤችፒቪ (HPV) ጋር የተያያዙ አዲስ ካንሰር ተጠቂዎችን ያገኛሉ። የኤችፒቪ ክትባት ልጅዎን በሴቶች የማህጸን ጫፍ ካንሰርን፤ በሴቶች እና ወንዶች ደግሞ በአፍ እና ጉሮሮ ውስጥ የሚገኙ ካንሰሮችን ጨምሮ ከዘጠን ከኤችፒቪ ጋር ታዛማጅ (HPV-associated) ከሆኑ ካንሰሮች እንዲከላከል ይረደዋል። እንደወላጅነትዎ/አሳዳጊነትዎ ልጅዎ ከበሽታ ነጻ እንዲሆን በርካታ ውሳኔዎችን ይወስናሉ። ኤችፒቪ ንBeing informed about (HPV) በሚመለከት መረጃ ማግኘት ጠቃሚ ውሳኔ ነው። የኤችፒቪ ክትባት አደጋ የሌለውና ልጅዎን ከካንሰር የሚከላከል ሲሆን፤ ለቫይረሱ ከመጋለጡ በፊት ለልጁ ከተሰጠው የበለጠ ውጤታማ ይሆናል። ክትባቱ ከሌሎች ከሚመከሩ ክትባቶች ጋር አንድ ዓይነት ጊዜ ሊሰጥ የሚችል ሲሆን የክትባት ሂደቱ ሲጀመር ልጁ እንደነበረው ዕድሜ ታይቶ በ ሁለት ወይም ሶስት ተከታታይ መጠኖች ሊሰጥ ይችላል። ተከታታይ ክትባቶቹን ማጠናቀቅ ጠቃሚ ነው።

እባክዎ ከዚህ ደብዳቤ በስተጀርባ የሚገኘውን መረጃ ይመልከቱ። መረጃውን ካነበቡ በኋላ እንደወላጅነትዎ/አሳዳጊነትዎ ልጅዎ እንዲከተብ ወይም የትምህርት ቤቱን የኤችፒቪ (HPV) ክትባት መስፈርት ላለመቀበል ሊመርጡ ይችላሉ። ነገር ግን የዲሲ ጤና (DC Health) በበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ማዕከሎች (Centers for Disease Control and Prevention (CDC)) በሚመከረው መሰረት ልጆች እንዲከተቡ አጥብቆ ይመክራል።

ልጅዎ ተከታታይ ክትባቶቹን የሚያገኝበትን ጊዜ ለመወሰን የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪዎትን ያግኙ። ይህንን እድል ኤችፒቪ (HPV) እና ሌሎች ክትባቶችን በሚመለከት ከአገልግሎት ሰጪው ጋር ለመወያየት ይጠቀሙበት።

ተጨማሪ መረጃ ካስፈለግዎት የዲሲ ጤና ክትባት መርሃ-ግብር ን (DC Health Immunization Program) በስ.ቁ. (202) 576-7130 ያግኙ።

# ሂውማን ፓፒሎማቫይረስ

# (HUMAN PAPILLOMAVIRUS)

## ሂውማን ፓፒሮማቫይረስ (human papillomavirus (HPV)) ምንድነው?

ሂውማን ፓፒሎማቫይረስ (Human Papillomavirus (HPV)) የቆዳ ወይም የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ሚውከስ ሜምብሬኖች (mucous membranes) ቁስለት የሚያመጣ የተለመደ የቫይሰሶች ቤተሰብ ነው። ከ100 በላይ የኤችፒቪ (HPV) ቫይረስ ዓይነቶች አሉ። የተለያዩ የኤችፒቪ (HPV) ኢንፌክሽኖች የተለያዩ የሰውነት እፍሎችን ያጠቃሉ። ለምሳሌ አንዳንዶቹ ዓይነቶች በ  For instance, some types can lead to abnormal cells on the በማህጸን ጫፍ (cervix)፤ በልቫ (vulva)፤ ፊንጢንጣ (anus)፤ የወንድ ብልት (penis)፤ አፍ፤ እና ጉሮሮ ላይ ያልተለመዱ ህዋሳት (abnormal cells) መከሰት የሚያመሩ ሲሆን አንዳንድ ጊዜም ወደ ካንሰር ያመራሉ።

## ምልክቶቹ ምንድን ናቸው?

ኤችፒቪ (HPV) ያለባቸው አብዛኛዎቹ ሰዎች ምልክቶች ወይም የጤና ችግሮች አያሳዩም። 90 በመቶ በሚሆኑት የሰውነት የበሽታ መከላከል ተፈጥሯዊ በሆነ ሁኔታ በሁለት ዓመት ውስጥ ኤችፒቪ ን (HPV) ያጸዳዋል።

## ኤችፒቪ (HPV) ምን ያህል የተለመደ ነው?

ኤችፒቪ (HPV) የተለመደ ነው። ብዙ ሰዎችን በህይወታቸው የሆነ እድሜ ላይ ያጠቃቸዋል። ብዙ ተጠቂዎች አያውቁትም። ብዙዎቹ የኤችፒቪ (HPV) ኢንፌክሽኖች (infections) ብዙ ጊዜ የሚቆይ የጤና ችግሮች ሳያመጡ በራሳቸው ጊዜ ይጠፋሉ። ይሁንና የትኞቹ ኢንፌክሽኖች ወደካንሰር እንደሚለወጡ ወይም የጤ ችግሮች እንደሚያመጡ ማወቂያ መንገድ የለም።

## ኤችፒቪ (HPV) የሚሰራጨው እንዴት ነው?

ለኤችፒቪ (HPV) መጋለጥ በማንኛውም ዓይነት ኤችፒቪ (HPV) ካለው ከማንኛውም ሌላ ሰው ጋር በሚደረግ የግብረ ስጋ ግንኙነት ሊከሰት ይችላል፤ የግብረ-ስጋ ግንኙነት የግድ አስፈላጊ አይደለም ነገር ግን ዋነኛው የተለመደ ቫይረሱን የማግኛ መንገድ ነው። ብዙውን ጊዜ ኤችፒቪ (HPV) የሚታዩ ምልክቶች ስለማይኖረው ማንኛውም ሰው ሳያውቀው ሊይዘው ወይም ሊያስተላልፍ ይችላል።

## ለኤችፒቪ (HPV) ህክምና አለው?

አንዴ ሰው ኢንፌክትድ (infected) ከሆነ ለ ኤችፒቪ ህክምና የለም። ነገር ግን ከኤችፒቪ ጋር ተዛማጅ ለሆኑ የብልት ማሳከኮች (genital warts) ለመሰሰሉ እና ሊያድጉ ለሚችሉ አንዳንድ ካንሰሮች ህክምናዎች አሉ። ብዙዎቹ ኢንፌክሽኖች በራሳቸው ይጠፋሉ። ይሁንና የትኞቹ ኢንፌክሽኖች ወደካንሰር እንደሚለወጡ ወይም የጤ ችግሮች እንደሚያመጡ ማወቂያ መንገድ የለም። **መከላከል ከህክምና የተሻለ ነው።**

## ኤችፒቪን (HPV) እንዴት መከላከል ይቻላል?

ኤችፒቪን (HPV) የመከላከያው የተሻለው መንገድ የኤችፒቪን ክትባት (HPV vaccine) መከተብ ነው። ክትባቱ በሴቶች የማህጸን ካንሰርን (cervical cancer) በውንድም በሴትም ደግሞ የብልት ማሳከኮችን (genital warts) እና ሌሎች ካንሰሮችን የሚያመጡ የኤችፒቪ (HPV) ዓይነቶችን መከላከል ይችላል።

## የኤችፒቪ (HPV) ክትባት አደጋ የለውም?

የኤችፒቪ ክትባት (HPV vaccine) አደጋ እንደሌለው ተመልክቷል። አሜሪካ ውስጥ የሚሰጥ ማንኛውም ክትባት ከምግብ እና መድሃኒት አስተዳደር (Food and Drug Administration (FDA)) ፍቃድ ከማግኘቱ በፊት በጣም ጥብቅ በሆነ ከአደጋ ነጻ የፍተሻ ሂደት ውስጥ ማለፍ ይጠበአበታል። ለእርሾ (yeast) ለህይወት በሚያስፈራ ሁኔታ አለርጂ (allergic) ያለባቸው፤ ወይም እርጉዝ የሆኑ፤ እንዲሁም ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ ህመም ያለባቸው ሰዎች ክትባቱን አይወስዱም። የክትባቱ ጎጂ ጎን መካከለኛ የክንድ ህመም፤ ትኩሳት፤ እና ክትባቱ የተሰጠበት የሰውነት ክፍል አካባቢ የመቅላት እና ህመም መሰማትን ሊያካትት ይችላል።

## የኤችፒቪን (HPV) ክትባት ማነው መውሰድ ያለበት?

ውጤታማ ለሆነ የኤችፒቪ ካንሰሮችን መከላከል ወንዶች እና ሴቶች የኤችፒቪን ክትባት (HPV vaccine)  በ11 ወይም 12 ዓመት እድሜ መውሰድ እንዳለባቸው ዶክተሮች ይመክራሉ። ክትባቱ ከ9 ዓመት ጀምሮም ሊሰጥ ይችላል። ክትባቱ ከ15 ዓመት በፊት ከተጀመረ በሁለት መጠኖች ሊሰጥ የሚችል ሲሁን በመጠኖቹ መካከል ከ 6 እስከ 12 ወራት እርቀት በማድረግ ማለት ነው። ዘግይተው የክትባቱን ሂደት የጀመሩ በአስራዎቹ እድሜ ያሉ ልጆች ወይም ደግሞ ደካማ የበሽታ መከላከል ያላቸው ልጆች 3 መጠን ያስፈልጋቸዋል።

*ክትባት የማህጸን ጫፍ ካንሰር ምርመራን (cervical cancer screening) የሚተካ አይደለም። ይህ ክትባት የማህጸን ጫፍ ካንሰር ከሚያመጡ ሁሉም ዓይነት ኤችፒቪ (HPV) ይከላከላል ማለት አይደለም። ሴቶች ተከታታይ የማህጸን ጫፍ ምርመራ (Pap tests) ማድረግ ይኖርባቸዋል።*

## ልጄን ከ ኤችፒቪ በሽታ (HPV disease) እንዴት መከላከል እችላለሁ?

ለመከተብ ጊዜ አይስጡ። ከጤና እገልግሎት ሰጪዎ ጋር ዛሬውኑ በመገናኘት ወንድ ልጅዎን ወይም ሴት ልጅዎን ከ ኤችፒቪ ኢንፌክሽን (HPV infection) ስለሚከላከሉበት ሁኔታ ይነጋገሩ።

## ተጨማሪ መረጃ ከየት አገኛለሁ?

- የጤና እገልግሎት ሰጪዎ
- የዲሲ የጤና ክትባት መርሃ-ግብር (DC Health Immunization Program) በ ስ.ቁ. (202) 576-7130
- የበሽታ መቆጣጠር እና መከላከል ጣቢያዎችን (Centers for Disease Control and Prevention (CDC)) በስ.ቁ. 1-800-CDC-INFO (1-800-232-4636) ወይም በድረ-ገጽ www.cdc.gov/hpv

## የመረጃው ምንጮች

የአሜሪካ የማህጸን ሃኪሞች ኮሌጅ የጎልማሳ ጤና ክብካቤ ኮሚቴ ፤ ሂውማን ፓፒሎማቫይረስ (American College of Obstetrics and Gynecologists (ACOG) Committee on Adolescent Health Care, Fact Sheet: Human Papillomavirus) ■ www.acog.org

ሲዲሲ የክትባት እና መከላከል መረጃ ለወላጆች (CDC Vaccine Safety Information for Parents) ■ www.cdc.gov/vaccinesafety/populations/parents.html

ሲዲሲ ብሄራዊ የክትባቶች እና የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች ማዕከል፤ ኤችፒቪ ክትባት ጥያቄዎች እና መልሶች (CDC. National Center for Immunizations and Respiratory Diseases. HPV Vaccine-Questions and Answers). ■ www.cdc.gov/hpv/parents/questions-answers.html

የክትባት አፈጻጸም እና መረጃ ትብብር ድረ-ገጽ (Immunization Action Coalition's vaccine information website): ■ www.vaccineinformation.org

DC HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# ዓመታዊ የሂውማን ፓፒሎማቫይረስ (HPV) ክትባት ላለመውሰድ የመወሰን ማረጋገጫ (Opt-Out Certificate)

**የኤችፒቪ (HPV) ክትባት ላለመውሰድ የመወሰን ማረጋገጫን ፎርም የአሞላል መመሪያዎች (የተጠናቀቀውን ማረጋገጫ ለትምህርት ቤቱ ይመልሱ፤ ለወደፊት እንዲረዳዎት የመረጃውን ቅጂ ያስቀምጡ)**

**ክፍል 1፤** ከመፈረምዎ በፊት ኤችፒቪ (HPV) እና የ ኤችፒቪ ክትባትን (HPV Vaccine) በሚመከተ መረጃ የያዘውን ወረቀት ያንብቡ።

**ክፍል 2፤** የኤችፒቪን (HPV) መረጃ ካነበቡ በኋላ ወላጅ/አሳዳጊ (18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ) ይፈርም።

**ክፍል 2 የተማሪው መረጃ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| የትምህርት ቤቱ ስም፤ | | | |
| የተማሪው ስም፤ | | የትውልድ ቀን፡ | ክፍል፤ |
| አድራሻ፤ | ከተማ፤ | ዚፕ ኮድ፤ | ስልክ ቁጥር፤ |
| የጤና እንክብካቤ ሰጪው ስም እና አድራሻ፤ | ከተማ፤ | ዚፕ ኮደ፤ | ስልክ ቁጥር፤ |

**የልጄ የጤና እንክብካቤ አገልግሎት ሰጪ የኤችፒቪ ክትባት (HPV vaccine)መክሯል** **አዎ** ☐ **አይ** ☐

**በሂዩማን ፓፒሎማቫይረስ ኤችፒቪ (Human Papillomavirus (HPV)) ክትባት ላለመሰተፍ ዓመታዊ ውሳኔ**

ኤችፒቪ (HPV) ክትባት አስራ ዓመት እድሜ ላልደረሱ ሴቶች እና ወንዶች ከተሰጠ የማህጸን ጫፍ ካንሰርን እና የብልት ላይ ማሳከክን በመከላከል ረገድ ስላለው ጠቀሜታ መረጃ አግኝቻለሁ፤ መረጃውንም በሚገባ መርምሬአለሁ። በኤችፒቪ (HPV) መያዝ ያለውን አደገኝነት እና በኤችፒቪ እና በማህጸን ጫፍ ካንሰር፤ ሌሎች ካንሰሮች እና የብልት ማሳከኮች ጋር ያለውን ግንኙነት በሚመለከት መረጃውን ከመረመርኩ በኋላ ከላይ በስም የተጠቀሰው ተማሪ በኤችፒቢ (HPV) የክትባት መስፈርቶች እንዳይሳተፍ ወስኛለሁ። ክትባት እንዲሰጥበት በተመከረው ጊዜ ውስጥ በማንኛውም ሰዓት ውስኔዬን እንደገና በመመልከት አስፈላጊዎቹን ክትባቶች መፈጸም እንደምችል አውቃለሁ።

______________________________ ________________
የወላጅ/አሳዳጊ ወይም የተማሪው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ከሆነ ፊርማ ቀን

______________________________
የወላጅ/አሳዳጊ ወይም 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነውን ተማሪ ስም ይጻፉ